# የአማርኛ ልብ ወለድ ንጉሥ ነገሥት

**አዳም ረታ ከጎልዮ መፅሔት ጋር ያደረገው ቃለ መጠይቅ**

የዐማርኛ የፈጠራ ሥነ-ጽሑፍ በጉልህ ሊቆጠር የሚችል ዕድሜው ከመቶ ጥቂት አልፎታል፡፡ በነዚህ ዓመታት ውስጥ፣ እጅግም ብዙ ባይሆኑ፤ እጅግም ግን ጥቂት ያልሆኑ ደራሲያን፣ ገጣሚያን፣ ተውኔት-ጸሓፍያን፣ ሐያስያን እና ወግ-ደራስያን በብዙ ውጣ-ውረድ ውስጥ ኾነውም ጥበቡን አስኪያደውታል፡፡ በዐለፉት አንድ መቶ ዓመታት ውስጥ ትልቁ የኢትዮጵያ ፍሬአማ ጉዞ በምን ዘርፍ ውስጥ እንደሚገኝ ራሳችንን ብንጠይቅ፣ ለማወዳደር ያህል እንኳ፣ ከፊታችን ብቅ የሚሉ ቁሳዊ እና ኅሊናዊ ሀብቶች ምን ያህል እናገኝ ይሆን? ምናልባት፣ ከረጅም የማብሰልሰል ቆይታ በኋላ፣ ጥቂት እጩዎችን እናገኝ ይሆናል፡፡ የሆነው ሆኖ ግን፣ ለዕጩነት ሊቀርቡ ከሚችሉ ጥቂት ሀብቶቻችን መካከል፣ የዐማርኛ የፈጠራ ሥነ ጽሑፍ አንዱ የመሆንና፣ አከራካሪ ሊሆን ቢችልም፣ የኢትዮጵያ የመቶ ዓመቱ ትልቁ ፍሬአማ ጉዞ፣ ተብሎ በበላይነት ለመሰየም የተሻለ ይዞታ የሚኖረው ይመስላል፡፡ ይህን የምንለው ግን፣ ከአጠቃላዩ የሀገራችን ልዩ ልዩ ዘርፎች ዘገምተኛነት እና ፍሬ-ቢስነት አንጻር ነው እንጂ፣ ሥነ-ጽሑፋችንን ከራሱ ጎዞ አንጻር በመገምገም አይደለም፡፡
በዐማርኛ የፈጠራ ሥነ-ጽሑፍ የአንድ ምእት-ዓመት ጉዞ ውስጥ፣ እንደ ዘመናቸው፣ ጥቂት ግዙፋን ተከሥተዋል፡፡ እነርሱን እንደ ንጉሦች ብንወስድና ከመካከላቸው አንዳቸውን በንጉሠ-ነገሥት የመሰየም አስገዳጅ የ"ደረጃ መዳቢነት" መንፈስ ቢጠናወተን፣ ወደደንም፣ ጠላንም፣ ወንበሩን ለአዳም ረታ ከመስጠት የሚታደገን አይኖርም፡፡
አዳም ረታ መኖሪያውን በካናዳ ካደረገ ከራርሟል፡፡ ከሦስት ዓመታት በፊት "ይወስዳል መንገድ፤ ያመጣል መንገድ" የታተመ ሰሞን እና ከጥቂት ወራት በፊት "መረቅ" የተሰኘው ድርሰቱ በተመረቀ ጊዜ፣ አዳም ረታ በአዲስ አበባ ተገኝቶ ነበር፡፡ በሁለተኛው አጋጣሚ ሰሎሞን አበበ እና ሌሊሳ ግርማ አግኝተውት፣ ከትሁቱ ደራሲ ጋር ተጨዋውተዋል፡፡

ጎልዮ፡ ከሥራዎችህ መካከል አብዛኞቹን ከሀገርህ ውጪ እየኖርክ፣ ቋንቋህን እና ምናብህን ይዘህ ነው የሠራሃቸው፡፡ አንድ ደራሲ ከሀገሩ ከራቀ ጥበባዊ ፈጠራው ይጎዳበታል የሚል ክርክር አለ፡፡ አንተስ ምን ትላለህ?

አዳም፡ ከሀገርህ ስትወጣ ራስህን "ባዶ" አድርገህ አይደለም የምትወጣው፤ ሁሉን ነገር ትውስታህ ውስጥ ትይዛለህ፤ ያልፈታሃቸው ችግሮችም ይኖራሉ፤ እና ሙሉ ራስህን ይዘህ ነው የምትወጣው፡፡ እዚያ ሆነ ስትጽፍ፣ ወረቀት እና ብእር ከትውስታህ ጋር ነው የምትፈልገው፡፡ የኔም እንዲሁ ነው፡፡ በዚያ ላይ ያን ያህልምኮ ሩቅ አይደለም፤ በሰው ልጆች መሀል ብዙ ርቀት የለም፤ በጣም ብዙ ነገሮችን ትጋራለህ፡፡ እዚያም በሰዎች መሀል ነው የምትኖረው፣ ጫካ ውስጥ አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ ከሀገር ውጪ እየኖሩ መጻፍ ለኔ ችግር አልነበረም፡፡

ጎልዮ፡ ሥራዎችህ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች፣ ለምሳሌ ወደ እንግሊዝኛ፣ ቢተረጎሙ ውጤቱ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ? ከእኛ ባህል እና ቋንቋ ውጪ የሚገኙ አንባቢያን በአንተ ሥራዎች የኛን ያህል ስሜታቸው ሊያዝ ይችላል ይሆን? ወይስ ሥራዎችህ ከዐማርኛ ቋንቋ እና ከኢትዮጵያ ባህል ጋር በጽኑእ የተቆራኙ ናቸው?

አዳም፡ ሞክሬ አላየሁትም፡፡ ግን በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ ማውራት እንችላለን፡፡ ቋንቋ ወካይ ነገር ነው፤ በአንዱ ቋንቋ ውስጥ የተወከለው ነገር በሌላው ቋንቋ ውስጥ ከሌለ፤ እንዴት ሊወከል

ይችላል ልትል ትችላለህ? ግን ለእኔ እንደሚመስለኝ፣ የሀገሬን ሁኔታ በራሴ ቋንቋ ስገልጽ፣ ለመግለጹ እቀርባለሁ፣ ግን ሙሉ በሙሉ እገልጻለሁ ብዬ አላምንም። ለዚያም ነው ሳታቋርጥ በተከታታይ የምትሠራው። የታሪኮቹ ጭብጥ ቢለያይም፣ በተከታታይ የምትሠራበት ምክንያት፣ ቀደም ሲል የሠራኸው ድርሰት ምልአቱ ስለሚያጠራጥርህ ነው። እና ቋንቋ፣ እንኳን ያልኖርኩትን የባዕዱን ባህል እውነታ ይቅርና፣ ራሴ የኖርኩትንም አሟልቼ ልገለጽ አልችልም። በሌላ በኩል ደግሞ "ኢትዮጵያዊ" ማለትስ ምን ማለት ነው? ገበሬ ብሆንና ሞፈር፣ ቀምበር አጥምጄ የምኖር ብሆን ኖሮ፣ አንዳች ያህል "ኢትዮጵያዊ" የምትለው ነገር ሊኖር ይችል ነበር። አሁን ግን፣ ትምህርት ቤት ገብተህ፣ እንግሊዝኛ ተምረህ፣ እንግሊዝኛ መጽሐፍት አንብበህ ዐድገህ ስታየው፣ ምን ያህል ንጹሕ ኢትዮጵያዊ ነህ? ብዙ የተደባለቁ ነገሮች አሉ። እና ያን "ንጹሕነት" አላውቀውም።

ኀልዮ፡ ግን አንተስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ድርሰት ጽፈሕ ታውቃለህ?

አዳም፡ አንድ ሰሞን ሞክሬ ነበር፣ ግን በእንግሊዝኛ መጻፍ አያረካኝም። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ድርሰት ለመጻፍ፣ ምናልባት በእንግሊዝኛ ጭቃ አቡክተህ የዐደግክ መሆን ሊኖርብህ ይችላል። እንጃ ብቻ፣ እኔ እንዳሻኝ ላደርገው አልቻልኩም። ምናልባት፣ ተደጋጋሚ አርትዖት በመሥራት ድርሰቱን ወደምፈልገው ደረጃ ላመጣው እችል ይሆናል። ይህ ግን አልፌ ሥራ ነው፣ እኔ ደግሞ ሥራዎቼን ተደጋጋሚ አርያት ልሠራባቸው አልፈልግም፣ እንደ ወረዱ ማቅረብን እመርጣለሁ፣ ስህተቶቼን በመጠኑ ነው የማርመው።

ኀልዮ፡ እስኪ ስለ የሥር መርሐ-ግብርህ እና ዕለትህን እንደምን እንደምታሳልፍ ንገረን?

አዳም፡ አብዛኛውን ጊዜ ወይ አነባለሁ ወይ እጽፋለሁ - ወይም እተኛለሁ።

ኀልዮ፡ በዕለት፣ በጽሐፉ ሥራ ላይ የምታሳልፈው ረጅሙ ሰዓት ስንት ነው?

አዳም፡ አንዳንድ ጊዜ ዐሥር ሰዓታት ያህል ልቀመጥ እችላለሁ።

ኀልዮ፡ ጥብቅ መርሐ ግብር አለህ፣ በዚህ ሰዓት ጀምሬ፣ በዚያ እጨርሳለሁ ብለህ የምታስቀምጠው?

አዳም፡ የለኝም። መጻፍ ሲያሰኘኝ፣ ማንበቤን አቆምና መጻፍ እጀምራለሁ፣ ሲበቃኝ ደግሞ፣ ወደ ንባብ ወይ ወደ ኢንተርኔት ወይም ወደ እንቅልፍ እሄዳለሁ። እንጂ ከዚህ ሰዓት እስከዚያ ሰዓት፣ ከዚህ ቀን እስከዚያ ቀን እጽፋለሁ ብዬ የምይዘው ዕቅድ የለኝም።

ኀልዮ፡ ግን በጥቅሉስ፣ በዚህ ዓመት ይህ ሥራ መጠናቀቅ አለበት ብለህ ዕቅድ አትይዝም?

አዳም፡ እይዛለሁ። ለምሳሌ አሁን፣ "የስንብት ቀለማት" አለ። እርሱን በዚህ ዓመት አጠናቅቃለሁ እላለሁ። ከፋፍዬ ግን ዕቅድ አልይዝም።

ኀልዮ፡ አንዳንድ ደራሲዎች ጥብቅ መርሐ ግብሮች አሏቸው። እንዲያውም በአንድ ቀን ምን ያህል ቃላት እንደሚጽፉ የሚቆጥሩ ደራስያንም አሉ። በአንተ አመለካከት የፈጠራ ሥራ እና ጥብቅ መርሐ ግብር ግጭት አላቸው ወይ?

አዳም፡ እንደ ደራሲው ባሕርይ ነው፡፡ እኔ ግን በመርሐ ግብር መመራት አልፈልግም፡፡ ምናልባት፣ የመርሐ ግብር ባሪያ ሆነው ታርፈውና፤ ኋላኮ የጥፋተኝነት ስሜት በራስህ ላይ ልትፈጥር ትችላለህ፡፡ “ወይኔ፣ ዛሬ ሳልሠራ ቀረሁ” ምናምን እያልክ፡፡ ስለዚህ፣ እኔ መርሐ ግብሬን ሳይሆን፣ ርእሰ ነገሬን ነው የማየው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ይሄን አድርጌያለሁ፣ ማለት ከቻልኩ፣ ለኔ በቂዬ ነው፡፡ ከዚያ፣ ወጥቼ ቡና መጠጣት እችላለሁ፡፡

ጎልዮ፡ ከሥራዎችህ መካከል ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያልታተመ ያለ አይመስለኝም፣ ከ“አለንጋና ምስር” በቀር፡፡ እርስዋ ምን የተለየ ነገር ገጠማት?

አዳም፡ በድሚ የታተሙ እንዳሉ አውቃለሁ፣ ግን በተናጠል የትኛው ሥራዬ ምን ያህል ጊዜ እንደታተመ በደንብ አላውቅም፡፡

ጎልዮ፡ አንድ ደራሲ የራሱን የአጻጻፍ ዘይቤ ይዞ በሚመጣ ጊዜ፣ ከእርሱ ዘይቤ ቀድሞ የነበረ ሌላ ገናና ዘይቤን ወይ ያፈርሳል ወይ ይበርዛል ወይም ሌላ፡፡ ለምሳሌ፣ የአዳምን ዘይቤ ለማጣጣም፣ የሐዲስ ዓለማየሁን ዘይቤ መተው ሊገባኝ ነውን?

አዳም፡ ስለዚህ ጉዳይ በደንብ አላውቅም ግን…

ጎልዮ፡ ማለት፣ የአንተ ድርሰት “የጨዋታ ሕግ” በቀድሞ ጊዜ አንባቢያን ተላምደውት ከቆዩት የድርሰት ቅርጽ፣ የተለየ ነው፡፡ እንዲህ ሁለት ዐይነት “የጨዋታ ሕግጋት” በሚገጥሙት ጊዜ ከአንባቢው ምን ይጠበቃል? አንዱን ጥሎ ሌላውን ማንሳት ወይስ ምን?

አዳም፡ የግድ አይደለም፤ አንዳንዴ ግን ሊያጋጥምህ ይችላል፡፡ ደራሲው በዘመኑ ከኖረበት እና የሕይወት ልምድ ከቀሰመበት የግሉም ሆነ የማኀበራዊ ኑሮ ልምዱ አንጻር የአተራረክ ዘይቤው ሊለያይ ይችላል፡፡ ሆኖም ከአንደኛው ዘመን ወደ ሌላው የሚሸጋገሩ አንዳንድ ቅሪቶች ይኖራሉ፡፡ የሐዲስ አለማየሁ ዘመን ከኃምሳ ዓመታት በፊት የነበረ ቢሆንም፣ አሁንም የሳቸውን ዐይነት የአተራረክ ስልት የሚጠይቁ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከ“ሀ” ተነስተህ “ፐ” ላይ የምትጨርስባቸው፣ ’ሊኒየር’ ስልት የሚጠይቁ ነገሮች፡፡ ስለዚህ ቅርጹ የተለወጠ ሌላ ዐይነት የአተራረክ ስልት ካልመጣ በቀር፣ የቀድሞው ስልት ይሄኛውን ዘመን ሊወክል አይችልም ማለት አይቻልም፡፡ የግድ አይደለም፡፡ አንድ አንባቢ ሁለቱንም ሊወድ ይችላል፡፡

ጎልዮ፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በአዲስ ነገር ጋዜጣ ውስጥ እንደጠቀስከው፣ በልጅነትህ ካነበብካቸው ልቦለዶች መካከል በታደሰ ሊበን አንድ መጽሐፍ ውስጥ ያገኘሃት አንዲት “ሌላው መንገድ” የምትል ርእስ እንዳስደነቀችህ ገልጸሀል፡፡ የአንተም ሥራዎች ርእሶቻቸው ለየት ያሉ ናቸው፡፡ ያቺ ርእስ በአንተ የርእስ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽእኖ አላት? በጥቅሉስ ለድርሰቶችህ አርእስት የምትሰጥበት የተለየ መንገድ አለህ ወይ?

አዳም፡ ያቺ ርእስ ተጽእኖ አላደረገቺብኝም፡፡ ርእስ ለመምረጥ ብዬ ብዙ አልለፋም፡፡ እያንዳንዱ ታሪክ የራሱን ርእስ የሰጥሃል፡፡ እኔ ርእስ ስሰጥ፣ ለአንባቢው ቀላል እና ቅርብ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ርእስ ሲሰጥ፣ ጥብቅ መሆን አለበት፡፡ ’አግሬሲቭ’ መሆን አለበት ይባላል፡፡ ያን አልፈልግም እኔ፡፡ በቃ ከድርሰቱ ውስጥ አንድ ቃል ፈልጌ ርእስ አደርገዋለሁ፡፡ አልጨነቅበትም፡፡

ጎልዮ፡ "ሌላው መንገድ" ስለምትለዋ የታደሰ ሊበን ርእስ ስታነሣ፣ 'ኬኦስ' እና 'ኦርደር' በውስጥዋ እንደያዘች ተናግረህ ነበር፡፡ እስኪ ትንሽ ግልጽ አድርግልን፡፡

አዳም፡ "ሌላው መንገድ" ስትል፣ ምርጫ የሚሰጥህ ይመስላል፡፡ ግን ሄ መንገድ ምን እንሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ በአንድ በኩል ፣ ታሪኩን በምታነብብ ጊዜ አለ፣ አንድ የዐለቀ ታሪክ ታገኛለህ፣ (ታሪኩ ምን እንደሆነ አሁን ትዝ አይለኝም)፣ ግን ደግሞ ይሄ መንገድ ሌላ እንደሆነ ነግሮሃል፡፡ ይሄኛው ሌላ መንገድ ከሆነ፣ ሌላ ደግሞ ያልተገለጸ መንገድ አለ ማለት ነው፡፡ እንደዚያ መሰለኝ፡፡

ጎልዮ፡ አንባቢዎችህ እንደራሳቸው ምርጫ፣ ከሥራዎችህ መካከል አብልጠው የሚወዱት አንድ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በአንተስ በኩል፣ በሆነ መልኩ ለየት አድርገህ የምታየው አለ?

አዳም፡ ምናልባት "ሌላው መንገድ"…

ጎልዮ፡ የለም፣ ከአንተ ሥራዎች መካከል ማለቴ ነው፡፡

አዳም፡ "ይወስዳል መንገድ፣ ያመጣል መንገድ" ምናልባት፡፡

ጎልዮ፡ ከሥራዎች መካከል በአንባብያን ዘንድ "ግራጫ ቃጭሎች" ብዙ ጊዜ ሲጠቀስ ይሰማል፡፡ ምክንያቱ ምን ሊሆን የሚችል ይመስልሃል?

አዳም፡ ስለ ልጅነት፣ ስለ ወጣትነት ስለሚናገር ሊሆን ይችላል፡፡ ዋዘኛ (አጫዋች) ስለሆነ ሊሆን ይችላል፡፡ የታሪኩ አፈሳሰስ ቀጥተኛ ስለሆነ ሊሆን ይችላል፡፡

ጎልዮ፡ እስኪ ሃይማኖታዊ ታሪክን ወደ ልብወለዳዊ ድርሰት ስለማምጣት እናንሣ፡፡ ለምሳሌ "እቴሜቴ" ውስጥ አዳም እና ሔዋን ላይ የተመረኮዘች አንዲት "በለስ" የተሰኘች የምወዳት ታሪክ አለች፡፡ ግን ሃይማኖታዊውን ታሪክ፣ በራስህ ምናብ ወደ ልብ ወለዳዊነት በምታመጣው ጊዜ ሃይማኖታዊ አውዱን አያስትም ወይ?

አዳም፡ ሤራው ሊቀየር ይችል ይሆናል፡፡ በታሪኩ መጨረሻ የሚወለደው ነገር ሐዘኔታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለሰው ልጅ ማዘን፣ ማልቀስ፡፡ ይህ ሌላው ጭማሪ ነው፡፡ ከገነት ይባረራሉ፣ ያለቅሳሉ፣ በወሲብ ይቀጣሉ፣ እና በሞት፡፡ የሰው ልጅ ይዞ የመጣው ግን ብዙ ጊዜ የሚሳተው የእርስ በእርስ መተዛዘን ነው፡፡ አንድ ችግር በሚከሠትበት ጊዜ ያ የሰው ዘር ይቀራረባል፡፡ ተፈጥሮን በመጋፋት ሊሆን ይችላል፣ አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚያደርሱት ችግርን በመቃወም ሊሆን ይችላል መተሳሰቡ፡፡ ዋናው ታሪክ ውስጥ የሌለ፣ በዚህኛው ውስጥ ግን የተጨመረ ነው ይሄ፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች ሐዘኔታን ከእግዚአብሔር ነው የሚጠብቁት፣ በራሳቸው መካከል አይጠብቁም፡፡ ከገነት ቢወጡም፣ የርስ በርስ መተዛዘን ግን እንደ አላቸው ይዘነጋሉ፣ ይሄ ሽልማት እንዳላቸው ይዘነጋሉ፡፡ እና ለቦለዱ የሚጨምረው ሰውአዊ ነገር አለ እንጂ የሚቀንሰው ነገር የአለ አይመስለኝም፡፡ ይሄ መጥፎ አይደለም፡፡ ሃይማኖት ግን ይሄን ይቀበል አይቀበል አላውቅም፡፡

ጎልዮ፡ እና እዚህ "በለስ" ትረካ ውስጥ ጀግና እንፈልግ ከተባለ ጀግና ማነው?

አዳም፡ ጀግና የለም፡ የሰው ልጅ ለሰው ልጅ መተሳሰቡ ነው ዋናው ነገር፡፡

ጎልዮ፡ ስለ ጥበብ እና ኅብረተሰብ ልጠይቅህ፡፡ በሥራዎችህ ኅብረተሰቡን ማስተማር ትፈልጋለህ? ወይስ ጥበብን ለጥበብነቱ ስትል ትሠራለህ?

አዳም፡ ብዙ ጊዜ ከማየው ነገር ተነስቼ ነው የምጽፈው፡፡ ግን ለመጻፍ ስነሣ ተዋረድ ይዤ አልነሳም፣ ለጥ የአለ ሜዳ ይዤ ነው የምነሣው፡፡ ሁሉም ነገር እኩል ነው ከሚለው እነሣለሁ - ዕቃም ይሁን ሰው፣ ሹምም ይሁን ባሪያ፣ ምንም ይሁን ምን፡፡ ከዚያ ለጥ ከአለ ሜዳ ላይ አንድ ገጸ-ባሕርይ ትወስዳለህ፣ እንደ ነቁጥ ዐይነት፡፡ ቀጥሎ ያ ራሱ የሚጠራልህ ነገር አለ፣ አንድ ግለሰብ አንድ ሰው ብቻ አይደለም፣ ከግለሰቡ የሚወጡ ብዙ ተወንጫፊ መስመሮች (ቬክተሮች) አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሕፃን መረጥክ፡፡ ሕፃኑ ያለቅሳል፡፡ ለምን ያለቅሳል? ከረሜላ ፈልጎ፡፡
እና እኔ የማደርገው ነገር ምንድን ነው፡- ከአማራጮቹ መካከል የምፈልገውን ገጸ-ባሕርይ መምረጥ፣ ከገጸ-ባሕርዩ የሚወጡ መስመሮችን መከተል፣ የሚያልቅበትን ቦታ መወሰን ነው፡፡ የትረካ ቅርጹን ነው እኔ የምፈጥረው፡፡ እንጂ በውስጡ ሊነሱ የሚችሉ ግብረገባዊ እና ሌሎች ነገሮች እኔ የምፈጥራቸው አይደሉም፣ ዓለም የሚሰጠኝ ነው፡፡ እኔ ኅብረተሰቡ ውስጥ የምገኝ ብሆንም፣ በምጽፍ ጊዜ ግን ራሴን ነጥዬ ነው፣ ገለል ብዬ ለመመልከት እሞክራለሁ፡፡ እንዲህ ብቻ ከሆንኩ ግን፣ ከመግለጽ በላይ ላልሄድ እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም ላይኛ-ገጽታን ብቻ በማየት ልወሰን ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ሁለተኛው ደረጃ እሸጋገራለሁ፡፡ ይህም ምንድን ነው፡- ገለልተኛ ታዛቢነቴን በመጣረስ፣ ወደ ገጸ-ባሕርዩ ውስጥ ለመዝለቅ እሞክራለሁ - ተዋንያን ‘ሜተድ አክቲንግ’ እንደሚሉት፡፡ ብዙ ጊዜ በ“አንደኛ መደብ” [“እኔ” እያለ በሚተርክ ገጸ-ባሕርይ] የምተርከው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እና ውስጡ ገብቼ፣ ያ ገጸ-ባሕርይ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት እሞክራለሁ፡፡ መገመት ማት ምናብ ሊሆን ይችላል፡፡ መገመት ማለት በወሰድኩት ገጸ-ባሕርይ አማካኝነት የማያቸውን ነገሮች ማስቀመጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ፣ ሁለት ነገሮችን ነው የማደርገው፡- በአንድ በኩል፣ እውነታውን ከውጪ ሆኖ መመለከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ወደ ገጸ-ባሕርዩ ውስጥ ዘልቄ የርሱን ስሜት መዘርገፍ፡፡ ትንሽ አስቂኝ ነገርም አለው፡፡

ጎልዮ፡ ግን ሳታውቀውም ቢሆን የራስህን ግብረ ገባዊ ምዘና ከማድረግ ልታመልጥ ትችላለህ?

አዳም፡ ሰርጎ ሊገባ ይችላል፡፡ ግን እንደዚያም ሆኖ በተቻለኝ መጠን ገለልተኛ ለመሆን እጥራለሁ፡፡ እኔ ኮምዩኒስት ብሆን፣ የምጽፈው ገጸ-ባሕርይ ደግሞ ካፒታሊስት ከሆነ፣ መጀመሪያ የማደርገው ነገር በእኔ እምነት ውስጥ ሆኜ እርሱን አለመመልከት ነው፡፡ ከዚያ ሰውዬውን ለማግኘት ወደ ውስጡ እገባለሁ፡፡ በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡

ጎልዮ፡ የዶስቶዩቭስኪም አንዱ ዐቅሙ ይሄ ነበር ይባላል፣ ሁሉንም ገጸ-ባሕርያት በእኩል ዐይን ተመልክቶ፣ ለሁሉም ድምፅ በእኩል ደረጃ መስጠት፡፡ ማለትም አንድ ጀግና አስቀምጦ ሌሎቹን ሁሉ በእርሱ ሥር መጨፍለቅ ሳይሆን፣ ለየገጸ-ባሕርያቱ ተመጣጣኝ ትኩረት መስጠት፣ ሁሉም የየራሳቸውን ድምፅ እንዲያሰሙ መፍቀድ - “ፖሊፎኒ” የሚባለውን ነገር ማምጣት፡፡ ከዚህ አንጻር ተዋጥቶልኛል የምትለው ድርሰት የትኛው ነው?

አዳም፡ ከባድ ነው፡፡

ጎልዮ፡ የዚህን ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እንደምን አገኘኸው?

አዳም፡ ብዙ አላነበብኩኝም፡፡ ግን በሐሜት ደረጃ የምትሰማቸው ነገሮች አሉ፡፡ ብዙ መጥፎ ድርሰቶች፣ ጥቂት ጥሩዎች አሉ ይባላል፡፡ በተለምዶ የሚባል ነገር ነው፡፡

ጎልዮ፡ እዚያ አታገኝም?

አዳም፡ አንዳንድ ነው የማየው፡፡ ያለቀ መልስ ልሰጥህ አልችልም፣ ምክንያቱም የተበታተነ እውቀት ነው ያለኝ፡፡ ጥቂት ነው ያነበብኩት፡፡

ጎልዮ፡ ለጽሑፍ ሥራ ከመቀመጥህ በፊት እንደ ማፍታቻ ወይም ማሟሟቂያ ምን ታደርጋለህ? አንዳንድ ደራሲዎች ለምሳሌ ሄምንግዌይ - ባለፈው ቀን የጻፉትን ያነባሉ፣ ሌሎችም እንደዚሁ የየራሳቸው ነገር የአላቸው አሉ፡፡ አንተስ?

አዳም፡ እንደ ልማድ ማለትህ ነው? ...ልብ ብዬ አላውቅም፡፡ እስኪ ወደ ኋላ ላጠንጥን፡፡ እቀመጣለሁ... ጽፍ ቶሎ ካልመጣልኝ ለሲጋራ ልነሳ እችላለሁ፣ መጻፍ ጀምሬ እምቢ ካለኝ ተነስቼ ልንጎራደድ እችላለሁ...

ጎልዮ፡ ትላንት የጻፍከውንስ ዛሬ ደግመህ የማንበብ ልማድ አለህ?

አዳም፡ የለኝም፡፡

ጎልዮ፡ ዛሬ ለጽሑፍ ከተቀመጥክ በኋላ ሙሉውን አንጠፍጥፈህ ባዶህን ነው ከጠረጴዛህ የምትነሣው ወይንስ ነገ ለምትጽፈው ነገር መነሻ የሚሆን ያህል ትተዋለህ?

አዳም፡ አንድ ምዕራፍ ስጽፍ፣ ከመጻፌ በፊት የምዕራፉ "ማፕ" ይኖረኛል፡፡ ይሄ ነው፡፡ ይሄን እንዲህ አደርግና እንዲያ አደርግና እዚህ ጋ እጨርሳለሁ እላለሁ፡፡ በመሀሉ የማነበው ነገር አጋጥሞኝ የሆነ ሐሳብ ሊመጣልኝ ይችላል፡፡ በማስታወሻ ትይዘዋለህ ወይም ልትረሳውም ትችላለህ፡፡ ...አንዳንዴ ላፕ-ቶፕ ተከፍቶ አንድ ቀን ሊቆይ ይችላል፡፡

ጎልዮ፡ በኮምፒዩተር ላይ ነው የምትጽፈው?

አዳም፡ በኮምፒዩተርም በወረቀትም፡፡ ሁለቱንም እጠቀማለሁ፡፡

ጎልዮ፡ ማለት እንደ ጀመርክ ትጨርሳለህ? ...መቅደድ፣ መጣል፣ ጀምሮ መተው... የለም?

አዳም፡ ሁለት ወይም ሦስት ሥራዎች ነው በአንድ ጊዜ የምሠራው፡፡ "መረቅ"ን እየሠራሁ "የስንብት ቀለማት"ንም እሠራ ነበር፡፡ አሁን "መረቅ" ስለሄደ ከ"የስንብት ቀለማት" ጋር ሌላ የዐጫጭር ልቦለዶች መድብል እየሠራሁ ነው፡፡ አንዱን እየጻፍኩ የመሰልቸት ስሜት ሲመጣ፣ ስለ ሌላው ማሰብ እጀምራለሁ፡- ታሪኮቹን እንዴት ማደራጀት እንዳለብኝ፣ ቅርጹ ምን መሆን እንዳለበት፣ ያለ ቅርጽ ለምን እንደዚያ እንደሚሆን - እነዚህን እያሰብኩ እናናለሁ፣ ያኛውን እረሳለሁ፡፡ እንዲህ ቆይቼ፣ በኋላ ወደዚያኛው ስመለስ፣ በደህና ጉልበት መሥራት እችላለሁ፡፡ ስለዚህ ሁለት ወይም ሦስት ሥራዎች ጎን ለጎን አድርጌ ካልሆነ አስቸጋሪ ነው፡፡

ጎልዮ [ሰአቸ]፡ የሌሊሳ አንድ መጽሐፍ ላይ ትንሽ ‘ብሰርብ’ ነገር ጽፈሐል፡፡ መጠናት ያለበት ነገር እንዳለ ጠቁመሃል፡፡ ትንሽ ግልጽ ታደርገው?

አዳም፡ ስለ “አንኮንሸየስ” ነዋ፣ ስለ ሕልም ነው፡፡ የተወሰኑ ታሪኮችን አንብቤያለሁ፣ ‘ፋሲኔቲንግ’ ናቸው፤ እንደዚህ ዐይነት ነገር ከዚህ በፊት አልተጻፈም፡፡ ጥሩ ሳይኮአናሊስት እና የሥነ-ጽሑፍ ሰው እነዚያን ሕልሞች ቢተነትን፣ ብዙ የሚገኝ ነገር አለ፡፡ ጥናት ያልኩትም ይሄን ነው፡፡

ጎልዮ፡ አንዳንድ ደራሲያን የግል ልምዳቸው ላይ በመመርኮዝ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡ ለምሳሌ ዶስቶዬቭስኪ የቁማር ልምዱን፣ ሄምንግዌይ የጀብዱ ልምዱን እና የመሳሰሉት፡፡ በሥራዎችህ ውስጥ የአንተ የግል ታሪክ ወይም ልምድ ምን ያህል አለ? እስካሁን ብዙም በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

አዳም፡ ምናልባት እኔ ‘ፕራይቬሲዬን’ መጠበቅ እፈልግ ይሆናል፡፡ የግሌን ታሪክ አልጽፍም፡፡ ግን ተሞክሮዎች ይኖሩኛል፡፡ አንድ ገጽ ሞክሮ ቢኖረኝ፣ ሦስቱን መስመር ከራሴ ተጠቅሜ ሌላውን ልብ ወለድ አደርገዋለሁ፡፡

ጎልዮ፡ ስለ የግል ተሞክሮ የጠየቅኩህ፣ አንድም ወደ አብዮት ዘመን ልወስድህ ፈልጌ ነው፡፡ በድርሰቶችህ ውስጥ የዚያ ዘመን አብዮተኞች ግብረገባዊ ዝቅጠት ውስጥ የወደቁ ሆነው ነው የምናገኛቸው፡፡ ይህን በተመለከተ ምን የምትለን አለ?

አዳም፡ ይሄ ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ ብዙ መርሳተ የምትፈልገው ነገር አለ፡፡ ግን ያው በጊዜው የነበረውን ነገር ነው ለመናገር የምሞክረው፡፡ ጥሩ ጊዜ አልነበረም፡፡ የተታለለ ትውልድ ነበር፣ ግን “ተታለልኩ” ብሎ ማንም አይነግርህም፡፡

ጎልዮ፡ ወደ እንጀራው ንድፈ ሐሳብ እንምጣ፡፡ ሥራዎችህን ከንድፈ ሐሳቡ አንጻር ባታያቸው ኖሮ ምን የሚጎድል ነገር ይኖር ነበር?

አዳም፡ ምንም አይጎድልም፡፡ ግን ግፊት አለ፡፡ ሰዎች “ፍልስፍናህ ምንድን ነው?” ብለው ይጠይቃሉ፡፡

ጎልዮ፡ ስለዚህ ሁለት ሥራ ለመሥራት ተገድደሃል?

አዳም፡ የሚያደክም ነገር አለው… ማድረጉን አልፈልግም ነበር፡፡

ጎልዮ፡ ለአንተ የድርሰት ቅርጽ እንጀራን ጥሩ አምሳያ ሆኖ አግኝተኸዋል፡፡ እንዴት ነበር የተከሰተልህ?

አዳም፡ ሁሉም “ኦርጋኒክ” እና “ኢንኦርጋኒክ” ነገሮች የተሠሩት ተመሳሳይ “ሞለኪውላር” መዋቅር ባላቸው ነገሮች ነው፡፡ እንጀራም ያን ይመስላል፡፡ ሆላንድ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ፣ ለዐምስት ዓመታት ያህል እንጀራ ሳልበላ ቆይቼ ነበር፡፡ እና አንድ ቀን እንጀራ ለመብላት ሄድኩ፡፡ ከዚያ ሳየው ዐዲስ ነገር ሆነብኝ፡፡ እና ጥያቄ መጠየቅ ጀመርኩኝ፡፡ እንጀራ ከጥንት

ጀምሮ የነበረው ለምንድን ነው? እስከዛሬ ሰዎች ስለዚያ ባይጽፉም፣ ያለማቋረጥ እስከዛሬ ድረስ ለምንድን ነው ምግብ ያደረጉት? ምግብነት ብቻ ሳይሆን፣ የሆነ ነገርም አለው አልኩ። ከዚህ ጥርጣሬ ተነሳሁና የእንጀራውን ቅርጽ ማየት ጀመርኩ። ከጂኦሜትሪ አንጻር ዐየሁት። እንዲህ እያልኩ ስሄድ ስለ የእንጀራ ታሪክ ማንበብ ጀመርኩ። የሚገርም ነበር። የሚገርም ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኛል። ከጠቢባን ጋር ይገናኛል፣ ከጥንታዊ 'ሴክሬድ ጂኦሜትሪ' ጋር ይገናኛል። ስለዚህ እንጀራን 'ሜታፎር' ማድረግ። በእንጀራ ውስጥ ያለው መዋቅር ላይ ወጥ ስታፈስስበት መረቁ በተለያዩ አቅጣጫዎች ነው የሚሄደው እንጂ በአንድ አቅጣጫ ከሀ ተነሥቶ ወደ ፐ አይሄድም። እኔም የምጽፈው በዚህ መልክ ነው።

ጎልዮ፡ እስኪ ስለ ዳኛቸው ወርቁ 'አደፍርስ' ንገረን። በልጅነትህ ካነበብካቸው ልብወለዶች አንዱ ነው። በአንተ ውስጥ ምን ቦታ አለው?

አዳም፡ ዳኛቸውን ያነበብኩት ድሮ ነው። በልጅነትህ አንድ ጥሩ ነገር ካጋጠመህ፣ ኋላ ቆይቶም፣ ዛሬም እንደገና ባገኘሁት ትላለህ። እንደ ናፍቆት ነገር ነው። ያኔ ከዳኛቸው ያደነቅኩለት ነገር ቃላቱን ነው። የምታውቀው ምን ዐይነት ባላገር ሆኖ፣ ግን ደግሞ ወደ አንድ እንግዳ ዓለም ይወስድሃል። ምናልባት ዛሬም ዳኛቸውን ዳግም ባነበው፣ ያን ማየት እፈልጋለሁ፣ ቃላቱን መማር እፈልጋለሁ። ከዚያ በላይ ግን 'አደፍርስ' አይናፍቀኝም። ...'ሀገር እንዲህ ተነሥቶ፣ እንዲህ ቢሆን፣ እንዲያ ቢሆን' የሚል ሐሳብ ላይ የአተኮረ ልብወለድ አልወድም።

ጎልዮ፡ ስለ ቃላት አነሳህልኝ። ጥሩ ነገር ላምጣልህ፡- በልጅነትህ "ፍቅር እስከ መቃብር" ቃላትን ለቅመህ ትርጉማቸውን ለማወቅ አባትህን ትጠይቅ ነበር። በዚህ ዐይነት ከ"አደፍርስ" ብዙ ሊኖሩ ነው።

አዳም፡ አዎን። ቃላት ደስ የሚሉ ነገሮች ናቸው። ብዘ ነገሮችን ይከፈፍቱልሃል። መዝገበ ቃላት እያገላበጥኩ አንድ ቃል በማገኝ ጊዜ፣ ሙሉ ልብወለድ ታሪክ ሲፀነስ ይሰማኛል። ይህ እንዴት እንደሚከሰት አይገባኝም። ግን፣ አንዲት ቃል ዐይተህ "ይሄ አንድ ታሪክ ይወጣዋል" ትላለህ። ቃላት ተአምራዊ ነገር አላቸው።

ጎልዮ፡ ስለ ሥነ-ጥበብ እና ነጻነት ምን ታስባለህ? ነጻነት ስልህ የሐሳብ ነጻነት ብቻ ሳይሆን፣ የኢኮኖሚ ነጻነትም ጭምር። ኑሮህ በገንዘብ እጥረት የተጎዳ ከሆነ፣ በፈጠራ ዐቅምህ ላይ ምን ተጽእኖ ያሳድራል? በባህልም በኩል እንዲሁ፣ ዝግ ኅብረተሰብ በሥነ-ጥበበኛው እንደምን ይታያል፣ የምናብ ነጻነቱ ላይ ምን ጫና ያሳድራል?

አዳም፡ "እንዲህ ነው" ለማለት ያስቸግራል። ግለሰቡ ዝግ ኅብረተሰብ ውስጥ ሆኖም ጥሩ ሊጽፍ ይችላል፣ ነጻ ኅብረተሰብ ውስጥ ሆኖም ደግሞ ጥሩ ላይጽፍ ይችላል። ይህ የሚወሰነው፣ ግለሰቡ በሚኖረው የልምድ ዐይነት ይመስለኛል። እንጂ ጥሩ ለመጻፍ ወይም ላለመጻፍ ቦታህ ብዙ ለውጥ አያመጣም። ትጽፋለህ። ይታተማል ወይስ አይታተምም? ሌላ ጉዳይ ነው። ብዘ እንቅፋቶች ሊኖሩት ይችላሉ፣ ግን ዝም ብለህ መጻፍ ነው። እንቅፋት ገጠመኝ ብለህ ከቆምክ፣ የአንተ ችግር ነው። ወረቀት እና ርሳስ አታጣም። መጥቶ ወረቀትህን ርሳስህን የሚነጥቅህ ከአለ ሌላ ጉዳይ ነው።

ጎልዮ፡ የገንዘብ ነጻነትስ፡- መኖሪያ፣ ምግብ፣ ልብስ ወዘተ?

አዳም፡ እነዚህ ለሰው ልጆች በሙሉ ያስፈልጋሉ፣ ለደራሲው ብቻ አይደሉም፡፡

ጎልዮ፡ እዚህ በምትኖርበት አካባቢ የሥነ-ጽፍ ማኅበረሰብ አለ? አንተስ ወጣ እያልክ ከሥነ-ጽሑፍ ሰዎች ጋር ትገናኛለህ? ወይስ አሁንም እንደ ልጅነትህ ጊዜ ብዙ አትጠጋም?

አደም፡ ልጅ ሆኜ እጠጋ ነበር፡፡ ተጠግቼ፣ ተጠግቼ በኋላ…፡፡ አሁን ብቻዬን ነኝ፣ ከማንም ጋር አልገናኝም፡፡ አንድ ቃለ ምልልስ ሰጥቼ ነበር ለአንድ መጽሔት፡፡ ሌላ የለም፣ አልገናኝም፡፡

ጎልዮ፡ በግላጭ መታየት አትወድም መሰለኝ?

አዳም፡ እንደዚያ ሊሆን ይችላል፡፡ ደግሞስ የጻፍኩት ነገር አንዴ ከወጣ በኋላ ማነኝ እኔ? ማንም አይደለሁም፡፡ እንደዚያ ስለሚመስለኝ ነው፡፡

ጎልዮ፡ ሰሞኑን አንድ ከአርተር ክስለር ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ እያነበብኩ ነበር፡፡ ደራሲው ብዙ ሥራዎችን ሠርቶአል፣ ግን ሁሌም ጥርጣሬ እንደአለው ይናገራል፡፡ አንተም ስለ ጥርጣሬ አንሥተሃል፡፡

አዳም፡ አዎን፣ ካልተጠራጠርክማ አልቋል ማለት ነው፡፡ ቅድም በአንድ ጊዜ ሁለት ወይ ሦስት ሥራዎች እንደማስኬድ ከተናገርኩትም ጋር ማያያዝ ትችላለህ፡፡ በጉልህ ባላውቀውም፣ የሆነ ጥርጣሬ ግን አለ፡፡ ድርሰቶቼም ውስጥ ብዚ ጊዜ ‘ይመስላል’ የሚል አገላለጽ ታገኛለህ፡፡ አጋጥሞኛል፣ “ምንድን ነው እንዲህ የምደጋግመው?” እላለሁ፣ ግን አላመልጠውም ቃሉን፡፡ እነዚህ ሁሉ ከጥርጣሬ የሚመነጩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፣ ይሄ ‘ሕጽናዊነት’ ያልኩህ ነገርም ከጥርጣሬ ጋር ይያያዛል፡፡ በተለይ ጨጫጭር ልብወለዶች ጭብጥህን ይቀንሱብሃል፡፡ እና ጉዳይህ እየጠበበ የመጣ ይመስላል፡፡ “በቀለ ወደ ቤቱ ሄደ” ብዬ አስቀምጥና፣ ደግሜ ሳስበው “ግን በቀለ ወደ ቤቱ ካልሄደስ? ወደ ሱቅ ቢሆንስ የሄደው?” ዐይነት ቅርንጫፎች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ቅርንጫፎች “ሕፅን” ይሆናሉ፡፡ እና ከመሠረቱ መላውን ሥራዬን፣ ለጥርጣሬዎቼ መፍትሔ የመፈለጊያ ሂደት፣ ብለህ ልትጠራው ትችላለህ፡፡ በዓለም ላይ ስትኖርም፣ እንደዚያ ይመስለኛል፡፡ እና ይሄ ጥርጣሬ ያልከው ነገር ሁልጊዜም እዚያው አለ፡፡

ጎልዮ፡ ቀደም ሲል ባልከው የወጡ አፈሳሰስ መንገድ ሁሉም ሥራዎች እርስ በእርስ መያያዝ አለባቸው? አፈንግጦ አልያዝም የሚል አይኖርም ወይ?

አዳም፡ ለምሳሌ፣ አሁን እየሠራሁት የምገኘው “የስንብት ቀለማት” ውስጥ፣ በሌላ ታሪክ ውስጥ የነበረ ገጸ-ባሕርይ ይመጣል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው፡- ያ ገጸ-ባሕርይ በቀድሞ ሥራ ውስጥ አለማለቁ ነው፡፡ ልክ እንደዚሁ፣ ለምሳሌ “ይወስዳል መንገድ፣ ያመጣል መንገድ” ውስጥ አንድን ገጸ-ባሕርይ ሌላም ቦታ ታገኘዋለህ፡፡ ይህን የማደረገው እንዲሁ ለመዘነጥ ወይም ለቅርጽ ብቻ ሳይሆን አንድ ገጸ-ባሕርይ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ስለአሉ ነው፡፡ አንድ የውሻ ገጸ-ባሕርይ ቢኖር ቢኖር፣ ከአንዱ ጋር ተናካሽ፣ ከሌላው ጋር ተጫዋች ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አጻጻፍ ተቃራኒ ጎኖችን አያይዞ ለመሄድ ያገለግላል፡፡
እና የወደፊት ፕሮጀክቴ ምንድን ነው፡- እስከዛሬ ድረስ የሠራኋቸውን ታሪኮች ሁሉ የተለያዩ ሥነ-ጽሑፋዊ መሣሪያዎች በመጠቀም፣ በአንድ ላይ ማያያዝ እና “ማግነም ኦፐስ” (ዐቢይ ሥራ) ማድረግ ነው፡፡ ሊሆን ይችላል ወይ? አላውቅም፡፡ ግን እሞክራለሁ፡፡ ከተሳካ፡፡ ወደ ሦስት ሺህ ገደማ ገጾች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ጎልዮ፡ ጽሑፌን ተመልከትልኝ፣ ገምግምልኝ የሚልህ የለም? እዚህስ ከመጣህ እንደዚያ ብሎ የጠየቀህ የለም?

አዳም፡ ብዙ ነገር ስለአለ ይከብደኛል፡፡ አንዳንድ ደራስያን እንዲህ አድርግልኝ ያሉኝ አሉ፡፡ ብዙ አይደሉም፣ ምናልባት ሁለት፣ ሦስት፡፡ የቻልኩትን አደርጋለሁ፡፡ ግን ጊዜ የለኝም… አለኝን ጊዜ ለራሴ ነው የማደርገው፡፡

ጎልዮ፡ ከፈጠራ ድርሰት ዐይነቶች የትኛው ይበልጥ ይማርክሃል?

አዳም፡ ግጥም ያው አልጽፍም፡፡ አንዳንዴ ግጥማዊ ስሜት ላይ በምሆን ጊዜ፣ እዚያው ድርሰቴ ውስጥ ‘ዝርግ ግጥም’ (ፕሮስ ፖዬም) እጽፋለሁ፡፡ ትንሽ እረካለሁ፡፡ …እና ግጥም አልጽፍም፣ ትንሽ ከበድ ይላል …እንደ ዝርው (ዝርግ) ድርሰት አያዝናናህም፡፡ በ‘ኔ ግምት ከጥበባት ሁሉ የሚበልጠው ጥበብ ረጅም ልብወለድ መጻፍ ነው፡፡ ሥነ-ግጥም ይበልጣል ይባላል፣ እኔ ግን ይበልጥ ነጻነት የሚሰጠኝ ረጅም ልብወለድ ነው፡፡ አይመስልህም?

ጎልዮ፡ ከዐጭር ልብወለድም ይበልጥብሃል?

አዳም፡ ይበልጣል፡፡ እንዲያውም አሁን፣ በ‘ኔ አመለካከት፣ ዐጭር ልብወለድ ከዚህ በፊት በነበረው ይዘቱ መቀጠል የለበትም፡፡ አንድ ብልጭታ ብቻ ነው የሚሰጥህ፣ ፍሰት የለውም፡፡ እኔ አንድ ዐጭር ልብወለድ ከጻፍኩ ብቻውን አልተወውም፤ ጥንድ መሆን አለባቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ፡፡

ጎልዮ፡ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ አድናቂዎችህ ብዙ ናቸው፡፡ እና አሁን እዚህ በመጣህበት እንበልና አንዱ አድናቂህ በድንገት አግኝቶህ፣ “አዳም ሆይ፣ አንተኮ የዐማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ንጉሠ-ነገሥት ሆነሃል” ቢልህ፣ ምላሽህ ምን ይሆን ነበር?

አዳም፡ እሸሻለኊ!

ጎልዮ፡ እ?

አዳም፡ ‘እግሬ አውጪኝ’ እላለሁ፡፡